CULTURAL HERITAGE PROTECTION HANDBOOK 1

# SECURITY AT MUSEUMS

# በሙዚየሞች ውስጥ ጥበቃ



UNESCO

## INTRODUCTION

- the following instructions are generally applicable in most circumstances.

- please note that the duties pictured here may be assigned to more than one guard.

- please remember that instructions issued by the Museum curator or other person in authority have priority over the indications of this manual.

- always trust your best experience, judgement and skill to handle unusual events or unforeseen circumstances.

## መግቢያ

- ከዚህ የሚከተሉት ትዕዛዞች በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው::

- ከዚህ ቀጥሎ ያሉት መመሪያዎች ለአብዛኛው ሁኔታ የሚጠቅሙ ናቸው::

- እዚህ ውስጥ የተጠቀሱት ተግባራትና ኃላፊነቶች ከአንድ በላይ ለሆኑ የጥበቃ ሠራተኞች ሊሰጥ እንደሚችል አስተውል

- በሙዝየሙ ኩሬተር ወይም ኃላፊነት ቦታ ላይ በሚገኝ ባለሥልጣን የሚሰጥ መመሪያ፤ በማኑዋሉ ላይ ከተመለከተው መመሪያ ቅድሚያ እንደሚኖረው አስታውስ፣ ባልተጠበቀ /ባልታሰበ/ ሁኔታ ለሚያጋጥም ወይም ለሚከሰቱ ሁኔታ መፍትሔ ለመስጠት የራስን ችሎታ/ክህሎትንና ማመዛዘኛ መተማመን::



Museum protection duties never stop – the handover from night duty to daytime duty should be carried out according to agreed procedures, in an orderly and secure manner.

የሙዝየም የመከላከል ተግባር የሚያቆም አይደለም፤ የጥበቃው ኃላፊነት ከማታ /ሌሊት ተረኛ/ ወደ ቀን ተረኛ ሲተላለፍ በተቀመጠ የአሠራር ሥርዓትና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል።



Duty starts about half an hour before opening to the public; all emergency exits should be free and the immediate exit area inspected to remove possible obstructions.

የሙዝየም ተግባር የሚጀመረው ሙዝየሙ ለሕዝብ ከመከፈቱ ግማሽ ሰዓት ቀደም ብሎ መሆን ይኖርበታል፤ ሁሉም የድንገተኛ አደጋ ጊዜ መውጫዎች ነፃ መሆን ይኖርባቸዋል፤ ወዲያውኑ የሚወጣባቸው አካባቢዎች እንቅፋት ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች ሁሉ ነፃ መሆናቸው ሊታይ ይገባል።



Open or unlock all windows and doors that have been secured at night.

ማታ /ሌሊት/ ለጥበቃ ተዘግተው የነበሩ በሮችንና መስኮቶችን ክፈት።




Check that all important keys are present or properly accounted for.

አስፈላጊ የሆኑት ቁልፎች ሁሉ በቦታቸው መኖራቸውን ተቆጣጠር/አረጋግጥ።



Read any remarks written in the log-book and take appropriate steps if any.

በሃሳብ መስጫ /ማስታወሻ ደብተር/ ላይ የተፃፉ ማንኛውም ዓይነት አስተያየት በማንበብ፤ እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ።



Switch off night intrusion detection panel and check regular operation of closed circuit television system, portable alarm transmitter, portable radio sets, public address equipment, first aid kit and emergency equipment.

ማታ ለጥበቃ መከታተያ በርተው የነበሩ መቆጣጠሪያ ፓናል ይጥፉ፤ የቴሌቪዥርን ሲስተም፣ በእጅ የሚያዙ የአደጋ ጥሪ አስተላላፊዎች /ትራንስሚተር/፣ በእጅ የሚያዙ ሬዲዩኖች፣ የሕዝብ መገናኛ መሣሪየዎች፣ የመጀመሪያ እርዳታ ቦርሳዎችንና የድንገተኛ አደጋ መሣሪያዎችን በትክክል መሥራታቸውን ማረጋገጥ።



Check the quality of the recorded images by replaying an accelerated video cassette or digital recorder.

በቴፕ የተቀዱ ምሥሎችን እንደገና በማጫወትና ፈጠን አድርጐ የሚያጫውት ቪዲዩ ካሴትንና ዲጂታል ሬኮርደርን በመጠቀም ጥራታቸውን አረጋግጥ።



Check your block note, pen, portable lamp and other personal equipment.

ማስታወሻ ደብተር፣ እስኪሪፕቶ፣ በእጅ የሚ ያዝ መብራት እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የግል ዕቃዎችንና መሣሪያዎች መኖራቸውን አረጋግጥ።



Inspect all artefacts on display and check that all are accounted for and secured.

በትርዒት ላይ ያሉ ቅርሶችን በጥንቃቄ በመመ ልከት፣ ሁሉም መኖራቸውንና በመልካም ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን አረጋገጥ::



If any artefacts are missing, check that the appropriate label, with duly authorized signature, is applied on site.

የገጎደሉ ቅርሶች ካሉ፤ ትክክለኛው ሌብል ተፅፎና ሥልጣን ባለው ሀላፊ ተፈርሞ በትክክለኛው ቦታ ላይ መደረጉን አረጋግጥ::



Look for artefacts accidentally moved or in a dangerous position; **do not touch artefacts.** Ask a specialist to rectify the situation.

ቅርሶች ሳይታወቅ ከቦታቸው ተንቀሳቅሰው ወይም በአደገኛ ሁኔታ መቀመጣቸውን ተመልከት፤ ይህ ዓይነት ሁኔታ ካጋጠመህ ቅርሶችን በጭራሽ አትንካ፣ የሚመለከተው ባለሙያ መጥቶ እንዲያስተካክላቸው ጥያቄ አቅርብ፡፡



Ask a specialist to rectify the situation; artefacts should always be moved by skilled people wearing gloves and taking special precautions.

የሚመለከተው ባለሙያ መጥቶ ሁኔታውን እንዲያስተካክል ጠይቅ፤ ቅርሶች ምንም ጊዜ ቢሆን መንቀሳቀስ ያለባቸው ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች ጓንት አጥልቀውና የተለየ ጥንቃቄ ወስደው መሆን ይኖርበታል፡፡



Please remember that water and fire are the two greatest risks in a museum.

ውሃና እሳት በሙዝየሙ ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሁለት ከፍተኛ አደጋዎች መሆና ቸውን አስታውስ::




Look for possible water damage.

ሊፈጠር የሚችል የውሃ አደጋን ለመመልከት ሞክር::



Avoid large piles of flammable packing materials; inform supervisor and ask for them to be removed.

ብዛት ያላቸውና ሊቀጣጠሉ የሚችሉ የማ ሸጊያ ማቴሪያሎችን ማስወገድ፤ ለበላይ ተቆጣጣሪው ማሳወቅና እንዲነሱ አድርግ፡፡



Check location of all portable extinguishers and …

በእጅ የሚያዙ ተንቀሳቃሽ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች በቦታቸው ላይ መሆናቸውን አረጋግጥና...



... state of operation.

... የአሰራር ሁኔታቸውን



Check location and state of fire alarm buttons.

የእሳት አደጋ ማንቂያ መሣሪያ /አላርም/ ቁልፎች ያሉበትን ቦታና መሥራታቸውን አረጋግጥ።



Check electrical connection wires and report any faulty or damaged wiring immediately.

የኤሊክትሪክ መስመሮችና ገመዶች ችግር እንዳለባቸው በማጣራት፤ የተበላሸ የኤሌክትሪክ መስመር መኖሩ ከታወቀ ወዲያውኑ ሪፖርት አድርግ።



Check the contents of all first aid kits installed in the exhibition rooms.

በኤግዚቢሽን ክፍሎች ውስጥ ያሉ የመጀ መሪያ እርዳታ መስጫ ማቴሪያሎች መሟላ ታቸውን አረጋግጥ።



Check that all internal phones are in working order.

ሁሉም የውስጥ ስልኮች የሚሠሩ መሆናውን አረጋግጥ::



Check the free field of vision of CCTV cameras.

ለCCTV ካሜራዎች ነፃ የሆነ የዕይታ መስመር መኖሩን አረጋግጥ::



Monitor cleaning operations and occasionally check contents of trash bins.

የፅዳት ሂደትን መከታተል፣ አልፎ አልፎም የቆሻሻ መጣያዎችን ፈትሽ፡፡



Report any bulbs that have blown.

የጠፉ /የተቃጠሉ/ አምፑሎችን ሪፖርት አድርግ፡፡



Fix minor disruptions, if possible, or report to appropriate service.

የሚቻል ከሆነ ትንንሽ ችግሮችን /ጥገናዎችን/ አከናውን፣ ወይም ለሚመ ለከተው የጥገና ክፍል አመልክት።



Check for any trash left on site and report to appropriate service .

በማሳያ /ትርዒት/ ቦታዎች የተተው ቆሻሻዎች መኖራቸን በመመልከት፤ ለሚመ ለከተው የፅዳት ክፍል ሪፖርት አድርግ።



Carefully identify visiting scholars and third parties, before granting a visitor pass, to be constantly displayed while on museum premises.

የጐብኝ ይለፍ ካርድ ከመስጠትህ በፊት የውጭ ተመራማሪዎች ሆነ ሶስተኛ አካላት በጥንቃቄ ለመለየት በመሞከር፤ በሙዝየሙ ቅርፅ ውስጥ እስካሉ ድረስ በአስፈላጊወ ቦታ ሁሉ እንዲያሳዩ አድርግ።



Closely monitor all loading and unloading operations.

የመጫንና የማራገፍን ተግባራት በቅርበት ተቆጣጠር።



Monitor and, if necessary, prevent activities, in immediate museum surroundings, that may be a source of danger – if appropriate, call police for help.

በሙዝየም አካባቢ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን መኖራቸውን ተከታተ ል፣ አስፈላጊ ከሆነ ለመከላከል መሞከርና፣ ተገቢ ከሆነ የፖሊስ እርዳታ ጠይቅ።



Monitor the activities of conservators, graphic artists and so on; if necessary, temporarily restrict access to the exhibition room where work is being performed.

የኮንሰርቬሽንና የግራፊክ አርት ባለሙያዎችን እንቅስቃሴ ተቆጣጠር፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጊዜያዊነትም ቢሆን የኤግዚቢሽን ሥራዎች የሚከናወንባቸው ክፍሎች እንዳይገቡ ከልክል /ከልክል።



If you use keys, giving access to showcases or other critical containers, do not let anybody handle the key on your behalf, or even see it.

የትርኢት ማሳያ ሳጥኖችና የሌሎች መያዣ ዎችን ቁልፎች የምትጠቀም ከሆነ፣ ሌላ ሰው አንተን ተክቶ እንዲይዝልህ አሳልፈህ አትስጥ፣ እንዲያይም አታድርግ::



Profile keys may be easily copied by making a quick impression with wax or soap.

የፕሮፋይል ቁልፎችን በሰም ወይም በሳሙና ላይ ቅርጻቸውን በመስራት በቀላሉ ኮፒ ማድረግ ይቻላል::



Even the codes of high security double bitted keys, used on safes, may be captured by a skilled observer.

ለካዝና የምንጠቀምባቸው ከፍተኛ ደብል የጥበቃ ቁልፎች ኮዶች እንኳን እውቀት ባለው ተመልካች ሊታወቁ/ሊያዙ ይችላሉ።



Be ready to open museum doors at stated time – it is an essential act of courtesy to visitors.

የሙዝየም በሮችን በተወሰነላቸው ጊዜ ለመክፈት ዝግጁ ሁን፣ ይሄ ለጐብኝዎች ያለህን አክብሮት የሚያሳይ አስፈላጊ ድርጊት ነው።



Gently but firmly, ask visitors to leave at the entrance all personal items that can cause damage to objects or may be used to hide and take these away.

በትህትና ሆኖም ግን ጠበቅ ባለ አነጋገር ጐብኝዎች የግል ዕቃዎቻቸው ቅርሶችን ሊጎዱ ስለሚችሉ ወይም ትንንሽ ዕቃዎች ቦርሳ ውስጥ ሊገቡ ስለሚችሉ በመግ ቢያው ላይ እንዲያስቀምጡ ጠይቅ፡፡



A museum is a temple of our cultural heritage - do not let unruly or improperly dressed visitors desecrate it.

ሙዝየሙ የባህላዊ ቅርሶች ቤተመቅደስ ነው፤ ሥርዓት የሌላቸው ወይም ተገቢ ያልሆነ ልብስ የለበሱ ጐብኚዎች እንዳያ ጐድፉት አያድርጉ፡፡



Be ready to help disabled visitors, giving assistance and directions – be careful not to be distracted from your main duty which is to protect exhibits.

አካል ጉዳተኛ የሆኑ ጐብኚዎችን አቅጣጫ በማሳየት ለመርዳት ዝግጁ ሁን፤ ሆኖም ግን ይህ ድርጊት ዋና ተግባርህ በሆነው የሙዝየም ትርዒቱን የመጠበቅ ተግባር ምንም እንዳያጓድል ተጠንቀቅ።



Keep an attentive eye on visitors during opening hours, to detect early signs of potential trouble or improper behaviour.

ምጉብኝት ሰዓት ያልተጠበቀ ችግር እንዳይ ፈጠርና ከሥነ ምግባር ውጭ የሆኑ ሁኔ ታዎች እንዳይኖሩ የጐብኝዎችን እንቅስ ቃሴ ቃኝ።



Try to find a strategic observation point and move often, constantly taking different paths and at different times.

ስትራቴጂካዊ የሆነ የመመልከቻ ቦታ ለመያዝ ሞክር፣ አዘውትረህ ተዘዋወር፤ የተለያዩ የጊዜ ልዩነት በመያዝ።



It takes only seconds to damage a painting with a portable spray can, or…

የሥነ ጥበብ ሥራዎችን በእጅ በሚያዙ ቀለሞች /ስፕሬዎች/ ለማበላሸት የሰኮንዶች ጊዜ ብቻ ነው የሚወስደው።



… to scratch a valuable portrait.

...ውድ የሆነ ምሥልን ለመፋቅ /ለመጧጠጥ



Prevent visitors from using flashes if photographing is authorized – explain that excessive light may irreversibly damage delicate organic-based colours and disturb other visitors.

ፎቶግራፍ ማንሣት ከተፈቀደ ጐብኚዎች የካሜራ ፍላሽ እንዳይጠቀሙ ከልክል፣ ብዙ ብርሃን መጠቀም ተፈጥሮአዊ ንጥረ ነገር በሆነ ማቴሪያል የተዘጋጀን ቀለም ሊመለስ በማይችል መልኩ ሊጐዳ እንደሚችልና የሌሎችን ጐብኚዎችም እይታ እንደሚረብሽ ግለፅ::



Prevent visitors from using tripods, during picture-taking (if authorized) – the tripod may interfere with the free flow of visitors and slow down rapid exit, in case of emergency.

ጐብኝዎች ፎቶግራፍ ማንሳት ከተፈቀደላቸው የካሜራ ማቆሚያ /ትራይፖድ/ እንዳይ ጠቀሙ ከልክል፤ ምክንያቱም ትራይፖድ ጐብኚዎች እንደልባቸው እንዳይንቀሳቀሱ የሚያግድና፣ በአደጋ ጊዜ በፍጥነት የመውጣት ሂደትን ሊያዘገይ የሚችል ስለሆነ ነው::



Do not let visitors touch artefacts of any kind – even metal can be damaged by corrosion from natural skin oils.

ጐብኚዎች ማንኛውንም ዓይነት ቅርሶችን እንዳይነኩ ከልክል፤ ሌላው ቀርቶ ብረት ነክ የሆነ ቅርስ እንኳን በተፈጥሮ ቆዳ ቅባት ምክንያት በዝገት ሊጐዳ ይችላል::



Strictly enforce a no-smoking policy; fire is a major risk for artefacts displayed in a museum .

በሙዝየሙ ውስጥ ሲጋራ ማጨስ እንደሌለበት ጥብቅ ሕግ ይኑርህ፣ ሙዝየሞች ውስጥ ለሚገኙ ቅርሶች እሳት ዋነኛው አደጋ ነው።



Gently yet firmly stop visitors from using exits which should be used only in emergencies.

በሥርዓቱ ነገር ግን ጠበቅ አድርገህ ጐብኚ ዎች በአደጋ ጊዜ ብቻ መውጫ የሆኑ በሮች እንዳይጠቀሙ ከልክል።



Do not allow visitors to bring food and bottles into the museum; bottles may break and food may spill on museum floors.

ጐብኝዎች ምግብና መጠጥ ሙዝየሞች ውስጥ ይዘው እንዳይገቡ መፍቀድ የለብህም፤ ምክንያቱም ጠርሙሶች ሊሰበሩ ይችላሉ፤ ምግብም በሙዝየሙ ወለሉ ላይ ሊንጠባጠብ ስለሚችል።



Show visitors where they may eat and drink – check that trash is thrown in bins.

ጐብኚዎች የት መብላትና መጠጣት እንዳለባቸው አሳያቸው፤ ትርፍራፊዎ ችንም ቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣላቸውን አረጋግጥ።



If you notice a suspicious bag or package in the museum ...

አጠራጣሪ የሆነ ቦርሳ ወይም ጥቅል በሙዝየም ውስጥ ከተመለከትህ...



... gently but firmly ask all visitors to leave, restrict access to the risk area and call for appropriate support.

በትህትና ነገር ግን ጠበቅ አድርገህ ሁሉም ጐብኚዎች ሙዝየሙን ለቀው እንዲወጡ ጠይቅ፤ አጠራጣሪ ወደሆነው ሥፍራ ማንም ሰው እንዳይቀርብ ከልክል፤ ተገቢውን እርዳታ ጥራ::



Young visitors are the future custodians of our cultural heritage, but…

ወጣት ጐብኝዎች የወደፊት ባህላዊ ቅርሶችን ተረካቢና ጠባቂ ናቸው፤ ነገር ግን…



… contact the school master, give advice and directions, discreetly monitor children's behaviour. If necessary, call for additional support.

የት/ቤቱን ኃላፊ አነጋግር፣ ምክር ስጣ ቸው፣ አቅጣጫ አሳያቸው፣ በድብቅ የልጆቹን እንቅስቃሴ/ፀባይ ተቆጣጠር፤ አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ድጋፍ ጥራ፡፡



Watch for children and visitors chewing gum; often the gum is found attached to the underside of artefacts.

ማስቲከ የሚያኝኩ ሕፃናትንና ጐብኝዎችን በጥሞና ተከታተል፣ አብዛኛው ጊዜ ማስቲካው በቅርሶች ማስቀመጫዎች ሥር ተለጥፈው ይገኛሉ።



Discreetly, but carefully, watch children's behaviour; the natural curiosity of children may lead to artefacts being touched or scratched, with possible consequential damage.

በድብቅ ነገር ግን በጥንቃቄ የልጆችን ፀባይ /ድርጊት/ ተከታተል፤ የህፃናት የማወቅ ፍላጐት/ጉጉት ፀባይ ቅርሶችን በእጃቸው በመንካትና በመቧጨር አደገኛ ሁኔታን ሊያስከትል ይችላል።




Please always remember that your primary duty is to protect the museum collection; if questioned by a visitor, give answers only related to museum facilities and rules; you are a guard, not a tourist guide.

እባክህ የመጀመሪያ /ተቀዳሚ/ ተግባርህ የሙዝየሙን ስብስቦች መጠበቅ እንደሆነ አስታውስ፣ በጐብኚ ጥያቄ ቢቀርብልህ እንኳን ምላሽ መስጠት ያለብህ የሙዝየሙን የውስጥ ፋሲሊቲና ሕጉን በተመለከተ ብቻ መሆን አለበት፣ አንተ የጥበቃ ሠራተኛ ነህ እንጂ /የጐብኝት ባለሙያ/ ጋይድ አይደለህም።



Keep an especially attentive eye on small items that can easily be removed, such as an antique vase cover, for instance, or ...

ለትንንሽና በቀላሉ ሊነሱ ለሚችሉ ቅርሶች ለምሳሌ ጥንታዊ የአበባ ማስቀመጫ ቫዝ ላይ የተለየ ትኩረት ስጥሠ።



… the hands of a clock, or…

… የግድግዳ ሰዓት መያዣ ወይም…



…a key and a keyhole cover.

… ቁልፍና የቁልፍ ቀዳዳ መሸፈኛ



Be ever alert and attentive; if you need to leave your duty post for a moment, ask to be replaced.

ሁልጊዜም ንቁና ቀልጣፋ መሆን ይኖር ብህል፣ ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ቦታህን ትተህ ለመሄድ ስትፈልግ ተተኪ ጠይቅ::



If no visitor is present, you may rest on appropriate collapsible chairs.

ምንም ጐብኝ ከሌለብህ፣ ተገቢው መቀመጫ ላይ ማረፍ ትችላለህ::



Never rest on artefacts on show.

በትርኢት ላይ ባሉ ቅርሶች ላይ በጭራሽ እንዳትቀመጥ/እንዳትዝናና።



Be always ready to use the internal phone to call for support.

ሆልጊዜም ተጨማሪ ድጋፍ ስትፈልግ የውስጥ ስልኮችን ለመጠቀም ዝግጁ ሁን።



Be always ready to use a portable fire extinguisher.

ሁልጊዜና በቀላሉ የሚያዙ የእሳት መከላከያዎችን/ማጥፊያዎችን ለመጠቀም ዝግጁ ሁን::



If a visitor should have an accident, ...

አንድ ጉብኝ አደጋ ቢያጋጥመው...



…keep other people at a distance and call for professional first aid.

ሌሎች ጐብኘዎች ራቅ እንዲሉ አድርገህ፣ የመጀመሪያ እርዳታ የሚሰጥ ባለሙያ ጥራ።



When the paramedics arrive, interview witnesses and record all the relevant facts.

ሐኪም ሲመጣ በአካባቢው የሚገኙትን ዓይን እማኞች ቃለመጠይቅ በማድረግ አስፈላጊውን/ተፈላጊውን መረጃ መዝግብ።



At appointed time, gently yet firmly escort all visitors to the exit.

የተወሰነ ሰዓት ሲደርስ በትህትና ግን ጠበቅ ባለ መልኩ ጎብኚዎች እንዲወጡ አድርግ፡፡



Strictly refrain from accepting gratuities of any kind; if appropriate, propose a donation to support museum activities .

ማንኛውንም ዓይነት ስጦታ ከመቀበል፤ ተቆጥብ ከተቻለ ለሙዝየሙ ሥራዎች ማከናወኛ ልግሥና/ስጦታ እንዲሰጡ ሀሳብ አቅርብ፡፡



Put all the museum exits under lock and key.

ሁሉንም የሙዝየም መውጪያ በሮች በቁልፍ ዝጋ::



Lock all windows.

ሁሉንም መስኮቶች ዝጋ::



Inspect all exhibition rooms.

ሁሉንም የኤግዚቢሽን ክፍሎች ፈትሽ።



Check all intrusion detector devices by observing the blinking light reaction to your movements (if appropriate).

የሰው እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ መሣ ሪያዎች ከምታደርገው እንቅስቃሴ ከሚሰ ጡህ ምላሽ ጋር በመከታተል መብራቶቹ በትክክል መስራታቸውን አረጋግጥ /ተገቢ ከሆነ/።



Inspect all service rooms and toilets.

ሁሉንም አገልግሎት መስጫ ክፍሎችና መፀዳጃ ቤቶችን ፈትሽ/ተቆጣጠር::



Check that all main keys are present or properly accounted for.

ሁሉንም ዋና ዋና ቁልፎች መኖራቸውንና በተገቢው መንገድ መቆጠራቸውን አረጋግጥ::



Write any information about your day shift in the logbook for the information of the night guards.

ማንኛውንም ስለ ቀን ሽፍት መረጃ፣ ስለ ማታ ጠባቂዎች በማስታወሻደብትር ላይ ፃፍ::



Turn on the night intrusion detection control panel; check that all security equipment is working properly.

የማታ ጣልቃ ገብ የመመርመሪያ የቁጥጥር ፓኔል መልስ ወይም ሁሉም የጥበቃ መሣሪያ በደንብ መስራታቸውን አረጋግጥ::



Perform night shift exchange of duties, according to relevant procedures.

ማታ ፈረቃ ስራ በምትቀያየሩበት ወቅት በተገቢው መመሪያ መሠረት ይሁን::



If appropriate, carry out the night shift watch tour by checking the areas for inspection in the sequence indicated here.

የሚያስኬድ ከሆነ የማታውን የጥበቃ ተግባር ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን ቦታዎች በሚከተሉት ቅደም ተከተል መሠረት ኅብኝ::



Check the important areas once again as indicated in this handbook.

በዚህ መፅሐፍ ላይ በተመለከተው መሰረት በጣም አስፈላጊ የሆነ ቦታዎችን በድጋሚ ተመልከት /አረጋግጥ፡፡



If there is a watch recorder, set to planned schedule.

ሰዓት መመዝገቢያ ካለ፣ በተወሰነ የጊዜ ሠሌዳ ማስተካከል፡፡

CLT/CH/MUS/06/17